# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter
Published by the Public Relations and Communication Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-6 መስከረም ወር 2010 ዓ.ም እትም

Volume-3 Number-6 September, 2017 G.C




- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከምስራቅ ጎጃም ዞን መስተዳደር ጋር በመተባበር በጮቄ ተፋሰስ ላይ የችግኝ ተከላ አካሂደዋል ፡፡
- በችግኝ ተከላው መርሃ ግብር የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንቶች እንዲሁም የዞኑ አስተዳዳሪና መምሪያ ሃላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡
- ችግኙ የተተከለው በጮቄ ተፋሰስ የአቫዛዣ ቀበሌ አባጅሜ ተፋሰስ ነው፡፡
- በቦታው ሃገር በቀልና ውጭ ሃገር ችግኞች የተተከሉ ሲሆን ከ1800 በላይ ሃገር በቀል ችግኞች ናቸው፡፡
- የአካባቢው ማህበረሰብ ችግኞችን እንዲንከባከብና ከእንስሳት ንክኪ እንዲጠብቅ ገለፃ ተደርጎለታል፡፡
- በ2008 ዓ.ም የክረምት ወራት በተሸረሸረ ቦረቦር መሬት የተተከሉት የኮሶ፣ ወይራና ሌሎች ሃገር በቀል ዛፎች በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ተጎብኝተዋል፡፡

## በውስጥ ገፆቻችን


- የ2009 በጀት ዓመት አጠቃላይ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ተካሄደ.....1
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አዲስ የተሻሻለ የመኖ ሳር ዝርያ ለአርሶ አደሩ አሠራጨ ......3
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከዘላቂ ልማት መካኑ-ጥናት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፕ አካሄደ .....5
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2009 ዓ.ም. ዓመታዊ የግንባታ ሥራዎች ግምገማ ተካሄደ....7
- የውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራ /Deliverology/ ስልጠና ተሰጠ......10
- የኢትዮጵያ ሶስዮሎጂስቶች፣ ሶሻል ወርከሮችና አንትሮፖሎጅስቶች ማህበር በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ወርክሾፕ አካሄደ....11
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከክረምት ተማሪዎች ጋር የዉይይት መድረክ አካሄደ....13
- የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሶስት አዳዲስ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የካሪኩለም ሪቪው አካሄደ.....14
- በምስራቅ ጐጃም ዞን የእንግጫ ነቀላ ሥነ-ሥርዓት ተካሄደ .....16
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ጋር በመሆን በጮቄ ተራራ የችግኝ ተከላ አከናወነ...17
- Leaders' Forum Evaluates the report of 2009 Plan Execution ...19
- Debre Markos University Distributes New Improved Grass Species to Farmers ...21
- Debre Markos University hosts a workshop on push-pull technology…….23
- Debre Markos University Launches more than ten New Under and Postgraduate Programmes in 2010……24

# ራዕይ
# Vision

እ.ኤ.አ. በ2025 ከአፍሪካ 10 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

**Debre Markos University strives to be one of the top ten Universties in Africa by 2025.**

# ተልዕኮ
# Mission

ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

**Producing competent, ethical and innovative graduates through providing quality instructional, Co-curricular and cultural involvement.**

አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

**Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders at local and national levels.**

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

**Providing demand driven community and consultancy services that contribute to the national development objectives.**

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እየተዘጋጀች ለአንባቢያን የምትደርሰው ወርሃዊ ዜና መጽሔት በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተካሄዱ የተለያዩ ሁነቶችን ዘገባ፣ የዩኒቨርሲቲውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ሌሎች ቁምነገሮችን አካታ ለንባብ ስትበቃ ቆይታለች፡፡

በዚህ እትም የመስከረም ወር 2010 ዓ.ም. ዜና መጽሔታችን በዩኒቨርሲቲው የተደረጉ ውይይቶችን በስፋት ዳሳለች፡፡ መልካም ንባብ!

ለወርሃዊ ዜና መጽሔታችን መሻሻል የእናንተ የአንባቢያን አስተያየት ወሳኝ በመሆኑ ለሚኖራችሁ ማንኛውም አስተያየት

በድረ ገጽ www.dmu.edu.et ወይም

በኢሜል dmu.cc2008@gmail.com አድርሱን!!

# የ2009 በጀት ዓመት አጠቃላይ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ተካሄደ ተካሄደ



ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት የአመራር ፎረሙን ሲመሩ

የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አመራር ፎረም የ2009 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ዙሪያ ግምገማ አካሄደ፡፡ ግምገማው የዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት በተሟሉበት ነሀሴ 4/2009 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሲካሄድ የ2010 ዓ.ም ዕቅድም ቀርቧል፡፡

አጠቃላይ የሁኔታ ግምገማ የተካሄደው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ አወያይነት ሲሆን በዩኒቨርሲቲዉ የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ባለሙያ የሆኑት አቶ አክሊሉ ጌታቸዉ በ2009 ዓ.ም የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርትና ዕቅድ አቅርበዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ክፍሎች በየደረጃው የተከናወኑ አጠቃላይ ተግባራትንና የነበረውን እንቅስቃሴ ሲቃኝ የነበሩትን የክህሎት፣የአመለካከትና የግብዓት ችግሮችን ለማካተት እያንዳንዱ ተዋናይ በየክፍሉ ያሳየውን ውስጣዊ ጥንካሬና ድክመቶች በአፈፃፀም ሪፖርቱ ተዳሷል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የትምህርት ጥራት አግባብነት፣ የምርምርና ማህረሰብ አገልግሎት፣ መልካም አስተዳደር፣ የአጋርነትና ህዝብ ግንኙነት፣ የሰራተኞችንና የተማሪዎችን ጥቅም ማሳደግ፣ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ የውስጥ ገቢን ማሳደግ፣ሃብት ምደባንና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ የደንበኞችንና አጋር አካላትን ቁጥርና እርካታን ማሳደግ፣ እና ሌሎች ጉዳዮች በሪፖርቱ የተነሱ ዓበይት ተግባራት ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከሰራቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት የተጠናከሩ የለውጥ ፕሮግራሞችን በመተግበር በዝግጅት፣ትግበራና ማጠቃለያ ምዕራፍ የተለያዩ ተግባራት ታቅደው በውጤታማ አፈፃፀም እንደተተገበሩ ተገልጿል:: በሰራተኞች ርብርብ፣ ጠንካራ የሰው ሀይል፣ የተሟላ ግብዓት፣ የተቀናጀ አመራርና ስልት ለትምህርት ሰራዊት ግንባታው ጉልህ ሚና እንደነበራቸው በሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

ሪፖርቱ የተከናወኑ ተግባራትን በጥንካሬና ውስንነት ያቀረበ ሲሆን ስራዎች በሁሉም ክፍሎች በዕቅዳቸው መሰረት በትብብር መሰራቱ፣ በሁለት ዙር አገራዊ የተሐድሶ ስልጠና መሰጠቱ፣ የሴት መምህራንና አመራሮች ቁጥር ማደጉ፣ የመምህራን የቡድን የምርምር ስራዎች ማደጉ እና ሌሎች ምርጥ ተሞክሮዎች በጥንካሬ የቀረቡ ስራዎች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙ ችግሮች የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሄ እየተሰጣቸው እንደሆነ ሪፖርቱ ዳሷል፡፡

የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ፣ መጠነ-ማቋረጥ መቀነስ፣ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማስፋትና መተግበር፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናከር፣ የውስጥና የውጭ ግንኙነቶችን ማጠናከር፣ ፕሮጀክቶችን በወቅቱና በጥራት መከታተል የሚሉት ደግሞ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንደሆኑ ተገልጧል፡፡

በመጨረሻም የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ ቀርቦ ገንቢ አስተያየቶችን በመቀበል እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ዕቅዱ ሲዘጋጅም ለትግበራው መሳካት የተለያዩ መነሻዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥንካሬዎችንና መልካም አጋጣሚዎችን በማጎልበት ከድክመቶችና ስጋቶች ደግሞ ትምህርት በመውሰድ የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ እንደሚቻል መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አዲስ የተሻሻለ የመኖ ሳር ዝርያ ለአርሶ አደሩ አሠራጨ

በእንደሻው ያዛቸው





አዲስ የተሻሻለ የመኖ ሳር ዝርያ ለአርሶአደሮች ሲሰራጭ

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል በደብረ ማርቆስ ከተማ አካባቢ ለሚገኙ አርሶ አደሮች አዲስ የተሻሻለ የእንስሳት መኖ ሳር ዝርያ አሠራጨ፡፡ ስርጭቱ በጐዛምን ወረዳ ስር በሚገኙ አራት ቀበሌዎች ከነሐሴ 09-10/2009 ዓ.ም. ተካሂዷል፡፡ ከወረዳ የግብርና ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ዴንሾና ሴታርያ የተባሉ ወደ 85,200 የሚደርሱ ነጠላ የመኖ ሳር ዝርያዎች እንደተከፋፈለ ታውቋል፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ዓለሙ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው፡፡ የመኖ ስርጭት በተካሄደባቸው ቀበሌዎች ተገኝተው ለወረዳ እና ለቀበሌ ባለሙያዎችና ለአርሶ አደሮች የመኖ አተካከሉንና እንክብካቤውን በተመለከተ ሲያስረዱ የተሻሻለው የመኖ ሳር ዝርያ የተፈጥሮ የመኖ ግጦሽ ለሰብል እርሻ እየዋለ በመምጣቱ

የእንስሳቱን ሐብት ሂደት ለማስጠበቅ ብሎም መሬቱንም ከሸርሸራ ለመከላከል የሚያስችል ከመሆኑም በላይ ለእንስሳት መኖነት ጎልህ ሚና እንዳለዉ ገልጸዋል፡፡

ለዚህም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአትክልት ሳይት/plant nursery/ በማዘጋጀት ወደ 10 የሚደርሱ ቋሚ የመኖ ሳር ዝርያዎችን ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ፍ/ሰላም፣ ስናንና ሌሎች አጐራባች ወረዳዎች በማስመጣት እያራባ እንደሆነ ዶ/ሩ አክለው ገልፀዋል፡፡

የመኖ ሳሩ በማንኛውም አካባቢ በጥቂት ውሃና ቦታ ሊራባ የሚችል በመሆኑ መሬትን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል በተወሠነ መሬት ላይ በማሳደግ ከብቶችን ሊያራባ ይችላል ብለዋል፡፡ በቀጣይም ከዞኑ የግብርናና እንስሳት ሃብት ጽ/ቤት ጋር በቅርበት በመነጋገር ለበርካታ ቀበሌ አርሶ አደሮች እውቅና ፈጥረው የመኖ ሳሩን በስፋት እንደሚያሠራጩ ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም የመኖ ሳሩ ለማንኛውም የከብት ዓይነት /ዝርያ/ የሚያገለግል ስለሆነ በጣም ሳይገረጅፍና የሳር ንጥረ ነገሩ ሳይባክን ታጭዶ ለከብቶች ሊሠጥ እንደሚባ ዶ/ር ብርሃኑ አሳስበዋል፡፡ የተሰራጨውን የሳር ዝርያም በቅርብ እንደሚከታተሉት ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል በጐዛምን ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ተጠሪ ጽ/ቤት የመኖና ስነ አመጋገብ ተወካይ አቶ እሱያውቃል ጥሩነህ በመኖ ስርጭቱ ወቅት ሲናገሩ በጐዛምን ወረዳ በተለይ የተመረጡት ቀበሌዎች በከብት ርባታ የታወቁ አካባቢዎች በመሆናቸው የተሠራጩት የዴንሾና ሴታሪያ የመኖ ዝርያዎች የበለጠ ለከብቶች መኖ እንደሚያገለግል ገልፀው አርሶ አደሩም ዝርያውን በቅንነት ተቀብሎ ለከብቶች መኖ እንደሚመግብ አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይም ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ እንደሚሠሩና ለምን ያህል ቀበሌ፣ አርሶ አደሮች እና የሳር ዝርያ እንደሚያስፈልጋቸው በዕቅዳቸው አካተው ተጠቃሚነታቸውን 50% እና በላይ እንደሚያደርሱ ተናግረዋል፡፡ የቀበሌ የግብርና ባለሙያዎችም በጥንካሬ እንደሚሠሩ ገልፀዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ከጐናቸው እንዳይለይ መልክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከዘላቂ ልማት መካነ-ጥናት ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፕ አካሄደ

በእንደሻው ያዛቸው



ረ/ፕሮፌሰር ገነት ደጉ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት አዉደ-ጥናቱን በንግግር ሲከፍቱ

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአቀንጭራ አረምንና አገዳ ቆርቁር ነፍሳትን ሊከላከል የሚችል የአባራሪና አጥማጅ /Push-pull/ ቴክኖሎጂን ለመተግበር አውደጥናት አካሄደ፡፡ በአውደ ጥናቱ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን ለተጠቃሚው ለማድረስም ስራ እየተሠራ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ በእንኳን ደህና መጣችሁና መክፈቻ ንግግራቸው ሲናገሩ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከያዛቸው ተልዕኮዎች አንዱ በሆነው በምርምር ዘርፍ ጉልህና ቀዳሚ የሆኑ የህብረተሰቡ ችግሮችን በመለየት በርካታ ስራ እየሠራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ በዚህም ዘርፍ በተመረጡ የምዕራብና ምስራቅ ጐጃም ዞን ወረዳዎች በተከሠተው የበቆሎን ተባይ ለመከላከል አባራሪና አጥማጅ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የተዘጋጀ ወርክሾፕ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከበቆሎ በተጨማሪም በሌሎች ሰብሎች ላይ ሊከሠቱ የሚችሉትን ተባዮች ግብርና ጽ/ቤቶች፣ አጋር አካላት፣ አርሶ

አደሮችና በቀበሌና በዞን የተሠማሩ ባለሙያዎች ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጥምረት በመስራት ቅድመ መከላከል ማድረግ እንዳለባቸውም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በወርክሾፑ ፅሁፍ ያቀረቡት ዶ/ር ተወልደብርሃን ገ/እግዚአብሔር የዘላቂ ልማት መካነ ጥናት አጋር አካል አውደ ጥናቱ የአፈር መከላትን የሚከላከል ወርክሾፕ እንደሆነ ገልፀው በተፈጥሮ ግብርና ላይ ያተኮረ ስርዓት-ምህድራዊ የተፈጥሮ ግብርናን ማሻሻል የሚያስችል ከተፈጥሮ ጋር የሚስማማ ግብርና፣ የአፈር ምርታማነትን የሚጨምር የግብርና ስርዓት፣ ምርታማነትን የሚጨምር አሰራር መሆኑን አስረድተልዋል፡፡ ይህም ሲሆን የአፈር ንጥረ ነገሮች ተጠርገው እንዳይሄዱ እንደየአካባቢው ሁኔታ በማጥናት ዘልማዳዊ የሆነውን የግብርና ስርዓት መቀየርም አንዱ የወርክሾፕ ዓላማ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

ሱ እድዋርድስ /Sue Edwards/ የዘላቂ ልማት መካነ-ጥናት አጋር አካልና የዶ/ር ተወልደብርሃን ገ/እዚአብሔር ባለቤት በወርክሾፑ ግብርና የተወሳሰበ ስርዓት ያለው ግን አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ግብርና ምርቶችን መጨመር የሚያስችል ዘዴን ሊቃኝ የሚችል ፕሮጀክት በመሆኑ መሬታችንን በአግባቡ በመጠበቅ ለአካባቢ ሙቀት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት የጥንት አያቶቻችንን ታሪክ ልንመለስ ይገባል በማለት ሃሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

ዶ/ር መስፍን አባተ እና ዶ/ር ብርሃኑ ዓለሙ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፕሮጀክቱ አባል ሲሆኑ ከንድፈ ሐሳብ ቅበላው እስከ አተገባበሩ ያለውን የአባራሪና አጥማጅ ቴክኖሎጅ አሠራርን በሰፊው አቅርበዋል፡፡ በገለፃቸውም በቆሎ በምዕራብና ምስራቅ ጐጃም ዞኖች በስፋት የሚመረት ምርት ቢሆንም አገዳ ቆርቁርና አቀንጭራ የአፈሩን ለምነት በመቀነስና በቆሎውን በቀጥታ በማጥቃት ምርታማነትን እየቀነሡት መጥተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና አጋር አካላት ጋር በመሆን በተገኘው የምርምር ዘዴ አባራሪና አጥማጅ /Push-pull/ ቴክኖሎጂ ዘዴን በመጠቀም ችግሮችን መከላከልና የአፈር ለምነትን መጨመር የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህ ዘዴም ሰብሎችን በስብጥር መዝራት እንደሆነ ከገለፃቸው ተረድተናል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኮሌጅ፣ ሁለት እጁ እነሴ፣ ደጀንና ጐዛምን እንዲሁም ከጃቢጠህናንና ፍ/ሰላም ከተማ አስተዳደር የምስራቅና ምዕራብ ጐጃም ዞን የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የዞንና የቀበሌ ባለሙያዎች፣ የዘላቂ ልማት መካነ ጥናት አጋር አካላት፣ ዘጠኙ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ቡድኑ አባላት፣ አርሶ አደሮችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የወርክሾፑ ተሳታፊዎች እንደነበሩ መረዳት ችለናል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2009 ዓ.ም. ዓመታዊ የግንባታ ሥራዎች ግምገማ ተካሄደ

በወርቅነሽ ደመም



የውይይቱ ክፊል ገጽታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2009 ዓ.ም. የግንባታዎች የሥራ እንቅስቃሴ በዩኒቨርሲቲው በሚሰሩ ከአስር በላይ ተቋራጮችና የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ነሐሴ 19/2009 ዓ.ም. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ተካሄደ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳይህ ካሣው የግንባታው የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ እየተገመገመ ጠንካራና ደካማ ጐኖች ላይ ሲወያዩበት የቆየ እንደሆነና አሁን ደግሞ በ4ኛ ሩብ ዓመት ዓመታዊ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት እየቀረበ ያለውን ስራ የሚገመግሙበት እንደሆነ በመክፈቻ ንግግራቸው ላይ ገልፀዋል፡፡ ተቋራጮችም እያንዳንዳቸው ሥራቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለና አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

ዮቴክ ኮንስትራክሽን በቡሬ ካምፓስ የመማሪያ ክፍል፣ ዶርሚታሪና ካፌ ለመገንባት የጀመረ ሲሆን መጠናቀቅ በነበረበት የጊዜ ገደብም በአንድ አንድ ምክንያቶች ግንባታው በወቅቱ መጠናቀቅ አልቻለም፡፡ አጠቃላይ የስራው እንቅስቃሴ ሲታይ በመጠናቀቅ ላይ ያለ



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በመሆኑ 89.17% ታቅዶ 85.53% እንደተከናወነና የተሻለ አፈፃፀም እንዳለው ከሪፖርቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡

አፍሮ-ጽዮን ኮንስትራክሽን ሎት 2 ደግሞ የጤናና ህክምና ካምፓስ ዶርሚተሪ፣ መማሪያ ክፍል፣ ቤተ-መጽሐፍት፣ ካፌና ኩሽና ለመገንባት በ22/10/2007 ዓ.ም. ሥራውን የጀመረ ቢሆንም በቁሳቁስ አቅርቦት ችግር፣ በሠራተኛ እጥረትና በመሳሰሉት በጊዜው ማጠናቀቅ አልቻለም፡፡ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴውም 70.14% ስለሆነ አፈፃፀሙም ዝቅተኛ እንደሆነ በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

3M ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽንም ዶርሚታሪ፣ መማሪያ ክፍል፣ ላቦራቶሪና የአስተዳደር ብሎኮችን ለመገንባት ስራውን ከአፍሮ ጽዮን ጋር በተመሳሳይ ወቅት በጤናና ህክምና ሳይንስ ካምፓስ የጀመረ ቢሆንም ስራው በተለያዩ ምክንያቶች በጊዜ ገደቡ መሠረት መጠናቀቅ አልቻለም፡፡ አፈፃፀሙ ሲታይም 40.74% ስለሆነ ዝቅተኛ መሆኑን በመግለጽ ሥራውን በተሻለ መልኩ ለመስራት ያልተሟሉ ግብዓቶችን ማሟላት፣ የሠራተኛ ቁጥር መጨመር እንዲሁም የባከነውን ጊዜ ለማካካስ ትርፍ ሰዓት መስራት እንዳለባቸውም በሪፖርታቸው ላይ ቀርቧል፡፡

ሌላው የግንባታ ተቋራጭ ፍሊንትስቶን ኮንስትራክሽን ሲሆን ፕሮጀክቱም በ22/11/2007 ዓ.ም. የተጀመረው የአስተዳደር ህንፃ ግንባታ ነው፡፡ የስራው እንቅስቃሴም አሁን የብሎኬት ሥራው አልቆ ልሰና ላይ እንደሆነና አፈፃፀሙም 46.50% እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ቀሪውን ስራም በወቅቱ ጨርሶ ለማስረከብ ጉዳዩን ትኩረት በመስጠት የሚያስፈልገውን ቁሳቁስና ሠራተኛ በማሟላት መስራት እንዳለባቸው እና ከባለፈው ዓመት ግምገማ ጋር ሲነፃፀርም የአሁኑ የተሻለ እንደሆነ በሪፖርታቸው ገልፀዋል፡፡

ታምራት ተመስገን ህንፃ ስራ ተቋራጭም እንደዚሁ የመምህራን መዝናኛ ግንባታን በ14/12/2007 ዓ.ም. የጀመረ ሲሆን እንደሌሎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራው ስለተጓተተ ተጨማሪ 413 ቀናት እንደተሰጡትና እስካሁን ሥራው 74.94% ቢከናወንም እንዳልተጠናቀቀ ከሪፖርቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ተቋራጭ የተማሪዎችን መዝናኛም በመገንባት ላይ ያለ ሲሆን አጠቃላይ የስራው እንቅስቃሴም 50.60% ተከናውኗል፡፡

ስራውን ከዚህ የበለጠ ለማከናወንም ያጋጠማቸውን የቁሳቁስና የሠራተኛ ችግር በመቅረፍ አፈፃፀማቸውን ከፍ ለማድረግ መስራት እንዳለባቸው በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

ሳፍር ኮንስትራክሽን ሎት 5 እና 6 ም ዓመታዊ የሥራ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ በድንበር ወሰን፣ በአመራር ችግር እና በመሳሰሉት ችግሮች ሥራው እንዳልተሠራና ከበፊቱ ለየት የሚያደርገው የኮለን ስራ መጀመሩ ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ዳንኤል ሱሊቶ ህብረት ስራ ተቋራጭ ሎት 4 የመማሪያ ክፍል ግንባታ ፕሮጀክቱን በ24/03/2009 ዓ.ም. የጀመረ እንደሆነና በ29/03/2010 ዓ.ም. ግንባታውን እንደሚያጠናቅቅ ውል የተያዘ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የስራው እንቅስቃሴም 35.12% የተከናወነ ሲሆን ከተጠቀሙት ጊዜ አንፃር ሲታይ ግን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላት ግን ያጋጠመውን የቁሳቁስ አቅርቦት ችግር እና የሠራተኛ ችግር በማስተካከል መስራት እንደሚገባቸው በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

ሌላው የግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ ዝቃላይ ጀኔራል ትሬዲንግ የጤና ካምፓስ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፕሮጀክት በ02/09/2009 ዓ.ም. ቁፋሮውን የጀመረ ሲሆን የሚያጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ደግሞ 12/01/2010 ዓ.ም. ቢሆንም ሥራው ከተጀመረ በኋላ ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ በዝናብ ምክንያት፣ በመንገድ ችግር እና በመሳሰሉት ሥራው ወደኋላ እንደተጓተተና በታቀደው እቅድ መሰረት ማከናወን እንዳልተቻለ ተገልቷል፡፡ ለወደፊት ግን እነዚህ ችግሮች በማስተካከል በተሻለ መልኩ በመስራት ሥራውን በወቅቱ ለማጠናቀቅ እንደሚጥሩ በሪፖርታቸው ላይ ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም በቀረቡ ሪፖርቶች ላይ አጠቃላይ ውይይት ተደርጎ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ከተሰጠ በኋላ ጠንካራ ጐኖች፣ መስተካከል ያለባቸው እና ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችም ተሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም አጠቃላይ የስራ አፈፃፀሙ ሲታይ በአብዛኛው ግንባታዎች ጥሩ አፈፃፀም እያላቸው መጨረስ ከሚገባቸው ጊዜ አኳያ ሲታይ ግን በተፈለገው ጊዜ ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡ ሁሉም ተቋራጮች ያሉባቸውን ችግሮች በመቅረፍ ግንባታውን በወቅቱ ለመጨረስ ተግተው መስራት እንዳለባቸው እና የከፋ ችግር ያለባቸውን ችግሮቻቸውን ፈትተው ወደ ውሣኔ እንደሚደርሱ ዶ/ር ሳይህ ካሣው በማጠቃለያ ንግግራቸው ገልፀዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራ /Deliverology/ ስልጠና ተሰጠ

*በስማቸው አየነው*



የስልጠናው ክፊል ገፅታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለዩኒቨርሲቲው መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች የውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራ (Deliverology) ላይ ስልጠና ተሰጠ፡፡

በዩኒቨርሲቲው የደሊቨሮሎጂ ፎካል ፐርሰን የሆኑት ዶ/ር አስካለማርያም አዳሙ እና አቶ አብይ ተጎዳ በስልጠና ወቅት ባቀረቡት የውይይት ፅሁፍ የትምህርት ጥራትን ችግር ለመቅረፍና የጥራት ደረጃን ከፍ በማድረግ እንዲሁም በሚሰጠው ስልጠና ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ተመራቂዎችን በማፍራት ሂደት ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመለየት በውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራ/ Deliverology/ ፅንሰ ሃሳብ መሰረት የቅድሚያ ቅድሚያ በመስጠት ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ የውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራ/ Deliverology/ በየደረጃው የሚገኙ የፐብሊክ ሰርቪስና የመንግስት የልማት ተቋማት አመራሮችና ፈፃሚዎች ቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ያቀዷቸውን ውጤት ተኮር እቅዶች በተቀመጡ የተግባር መከታተያ ስታንዳርዶች መሰረት በስኬታማነት ለማስተግበርና የታለመለትን ውጤት ለማስመዝገብ የሚከተሉት የአሰራር ስርዓት መሆኑን ገልፀዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ይህ ፍልስፍና ሌላ የለውጥ ትግበራ መሳሪያ ሳይሆን ሲተገበሩ የቆዩና በመተግበር ላይ ያሉትን የለውጥ ትግበራ መሳሪያዎችን ማለትም BSC; Kizen; cooperative learning እና BPR ትኩረት ሰጥተን እንድንሰራ የማድረጊያ ስልት እንደሆነ በገለፃቸው አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው የምሩቃንን የእውቀት፣የክህሎትና አመለካከት ደረጃ በማሳደግ ከዩኒቨርሲቲው ተመርቀው ከሚወጡ ተመራቂዎች ውስጥ 80% የሚሆኑትን በ12 ወራት ጊዜ ስራ ማስቀጠር ይኖርበታል በማለት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ ለትምህርት ጥራት መጠበቅ መምህራን ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የውጤታማነት አሰራር ስርዓት ትግበራን/ደሊቨሮሎጂ ስትራቴጅን በመተግበር ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲውም የሚያሰለጥናቸው ምሩቃን ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ የሚከፈቱ የትምህርት መስኮች ገበያው ከሚፈልገው የሰው ሃይል እውቀት፣ ክህሎትና ፍላጎት አንፃር የተጣጣመ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ ዋናው ትኩረት አፈፃፀም ላይ ከሆነ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡ ሰለዚህ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ደሊቨሮሎጂን ለመተግበር መረባረብ ይኖርበታል በማለት አሳስበዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ሶስዮሎጂስቶች፣ ሶሻል ወርከሮችና አንትሮፖሎጅስቶች ማህበር በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ወርክሾፕ አካሄደ




**ደ/ማ/ዩ፡**በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒትስ ኮሌጅ ሶስዮሎጂ ትምህርት ክፍል ከኢትዮጵያ ሶስዮሎጂስቶች፣ ሶሻል ወርከሮችና አንትሮፖሎጅስቶች

ማህበር ጋር በመተባበር ከሐምሌ14-16/2009 ዓ.ም የጥናትና ምርምር ክህሎትን ለማሳደግ በደ/ማ/ዩ የስብሰባ አዳራሽ ስልጠና አካሄደ፡፡

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማንቲስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የድህረ ምረቃ ፕሮግራም አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ኃይሌ ካሳሁን የስልጠና መድረኩን በንግግር ሲከፍቱ በጥናትና ምርምር ስራ ላይ የተሻለ ክህሎትና ዕውቀት መያዝ ለትምህርት ሰዎችና ተመራማሪዎች የጎላ ሚና እንዳለው ገልፀዋል፡፡ በገለፃቸውም ጥናትና ምርምር ማካሄድ በትምህርት ሙያቸው ላይ አዳዲስ የዕውቀት መሻሻሎችን መገብየት እንደሚችሉና ሌሎች ጠቃሚ የስልጠና መድረኮችን ማግኘት እንደሚችሉ አብራርተዋል፡፡ ዶ/ር ኃይሌ በንግግራቸው አክለውም የጥናትና ምርምር ስራዎች ባለሙያዎች የደረጃ እርከናቸውን ማሳደግ የሚያስችል ዋጋ እንዳለውም ተናግረዋል፡፡

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአንትሮፖሎጂ መምህር የሆኑት ዶ/ር አስቻለው አበበ ስልጠናው ሲሰጥ የስልጠናው አርዕስት ደግሞ  የጥናትና ምርምር ምንነትና ባህርያት፣ የአቀራረብ ዘዴዎች፣ ዓይነቶች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃ  አተናተን ስልቶች የሚሉትን አብይ ጉዳዮች አስረድተዋል፡፡ በሌላ በኩል በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ወርክ መምህር የሆኑት ዶ/ር ቀረብህ አስረስ በበኩላቸው የጥናትና ምርምር የፍልስፍና መሰረቶች፣ የምርምር አዘገጃጀት ሂደቶች፣ የመረጃና የናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ ትንተና እና ሌሎች ጉዳዮችን በስፋት አስረድተዋል፡፡

በስልጠናውም በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ምላሽ እንደተሰጠ ከስልጠናው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ሶስዮሎጂስቶች፣ አንትሮፖሎጅስቶች  እንዲሁም ሶሻል ወርከሮችና በነዚህ የትምህርት መስኮች የተመረቁ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በስራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ደግሞ የስልጠናው ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ በመጨረሻም ስልጠናውን በንቃት ተሳትፈው ለጨረሱ ሰልጣኞች የሰርቴፊኬት ሽልማት ተበርክቶ በግቢው በተለያዩ ቦታዎች የፎቶግራፍ ስነ-ስርዓት አካሂደዋል፡፡

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከክረምት ተማሪዎች ጋር የዉይይት መድረክ አካሄደ




**ደ/ማዩ**፡በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የርቀት ትምህርት ማስተባበሪያ ዳይሬቶሬት አስተባባሪነት ከክረምት ተማሪዎች ተወካዮች ጋር ዉይይት ተካሄደ፡፡

ዉይይቱን የመሩት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ሲሆኑ የዉይይት መድረኩ አወያዮች ደግሞ የተከታታይ ትምህርት ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ አስናቀዉ አዉክ፣ የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን አቶ ስሜነህ ዋሴ፣ የተፈጥሮና ኮምፑቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን አቶ ይልቃል በዜ፣ የህግ ትምህርት ቤት ዲን አቶ ወልደትንሳኤ ፈንቴ፣የ ተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ተስፋየ አለቃ፣ የቤተ መጽሃፍት ተወካይ አቶ አዝመራዉ እንዳለዉ እና የስነ-ትምህርት ተጠሪ ወ/ሮ መሰረት አለም ነበሩ፡፡

የዉይይት መድረኩ አላማ የክረምቱ ትምህርት በተመደበለትና በታሰበለት ጊዜ እንዲሰጥ  እና ተማሪዎችም መልካም ስነ-ምግባር ይዘዉ ያለምንም ችግር እንዲጨርሱ ለማድረግ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በትምህርት ሂደቱ ላይም አልፎ አልፎ የሚፈጠሩ ችግሮችን በወቅቱ በመፍታት መማር ማስተማሩን በተሳለጠ መንገድ ለማካሄድ እያንዳንዱ የግቢዉ ማህበረሰብ ተግቶ ሊሰራ እንደሚገባዉ ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ጨምረዉ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይም በየሁለት ሳምንቱ ከየኮሌጃቸው ሰራተኞች ጋር ዉይይት እንደሚያደርጉና የሚፈጠሩ ችግሮችን በጋራ ሊፈቱ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

አንዳንድ  ክልሎች ዩኒቨርሲቲዉና ትምህርት ሚኒስቴር ከመደበዉ የቁጥር መጠን በላይ ተማሪዎችን በመላክና አንዳንዶችንም በማዘግየት በምዝገባ ወቅት ለተፈጠረዉ ውስን ችግር  ዩኒቨርሲቲዉ በቻለዉ መጠን እንደቀረፋቸዉ ለተሳታፊዎች ተብራርቷል፡፡ ወደፊትም ቢሆን ዲኖች፣ ትምህርት ክፍሎች፣ ኮሌጆችና ሌሎችም ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊዉን ትብብር እንደሚያደርጉም አክለዉ ገልጸዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት፣ የቤተ-መጽሃፍት አጠቃቀም፣ የመምህራን፣ የተማሪዎች እና ሌሎች አገልገሎት ሰጭ ግለሰቦችና ተቋማት በጥንካሬና በድክመት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በዉይይት መድረኩ የተነሱ አበይት ነጥቦች ናቸዉ፡፡ በዉይይቱም በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዉ አወያዮች በሚመለከታቸዉ ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም ለመማር ማስተማር ሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት፣ ከመምህራን ጋር በመቀራረብና በመነጋገር፣ መረጃዎችን በአግባቡ ለሚመለከተዉ በማድረስና ችግሮችን ተወያይቶ በመፍታት በቀጣይ በጥሩ ሁኔታ መስራት እንደሚገባ ለአወያዮችና ለተማሪ ተወካዮች ዶ/ር ንጉሴ አሳስበዋል፡፡

# የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሶስት አዳዲስ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የካሪኩለም ሪቪው አካሄደ



ዶ/ር አሐዱ መንዝር የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ሲያደርጉ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በኮምፕዩተር ኢንጂነሪንግ፣ በሃይድሮሊክ ኢንጂነሪንግ እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን የውጭ ባለሙያዎችን ጋብዞ የካሪኩለም ሪቪው (curriculum review) አካሄደ፡፡

ዩኒቨርሲቲው አሁን ባለው መረጃ መሰረት ከ31 በላይ ስራ የጀመሩ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ያሉት ሲሆን በ2010 ዓ.ም ደግሞ ከ40 በላይ ፕሮግራሞች እንደሚኖሩት የድህረ ምረቃ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር አሐዱ መንዝር በፕሮግራሙ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው ላይ ገልፀዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ሲከፍት ሳይንስና ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ራዕዩን በታለመለት ጊዜ ለማሳካት የራሱ ሚና እንደሚኖረውም ዶ/ር አሃዱ አክለው ገልፀዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እነዚህን የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ለመክፈት ሲያስብ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ ተፈላጊነታቸው የጎላ መሆኑን፣ፕሮግራሙን ለማስኬድ በቂ የሰው ሃይል በኢንስቲትዩቱ መኖሩን እና ከሌሎች የትምህርት ክፍሎች አንፃር የተሻለ የላቦራቶሪ አቅርቦት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ፕሮግራሞችን መምረጥ መቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዩኒቨርሲቲው እነዚህ ፕሮግራሞች መከፈት ለዩኒቨርሲቲውም ሆነ ለአከባቢው ማህበረሰብ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ለዩኒቨርሲቲው ያለው ፋይዳ የመጀመሪያ ዲግሪ መምህራንን ቁጥር ዜሮ በማድረግ 75/25 ማለትም የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ቁጥር 75% ፣ የማስተርስ ዲግሪ መምህራን ቁጥር ደግሞ 25% ለማድረግ ያስችላል፤ የቴክኖሎጂ መምህራንን በስራ ቦታቸው ላይ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ለአካባቢው ማህበረሰብ ደግሞ የትምህርት እድል ይፈጥራል፤ የአካባቢውን የውሀ ማማ በመጠቀም የተለያዩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በምሁራኑም ሆነ በተማሪዎች ለመስራት ያስችላል፡፡

የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ ይህን ካሪኩለም ሲቀርፅ የተለያዩ መረጃዎችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እንዳገኘ የተገለፀ ሲሆን የሚከፈቱ ፕሮግራሞችን ይዘት፣ ስነ-ዘዴ፣ ክፍለ ጊዜ፣ አላማ፣ ውጤት አሰጣጥ እና የመሳሰሉትን በተመለከተ የሃይድሮሊክ ኢንጂነሪንግ በአቶ ሙሉ ሰውነት፣ የኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ በዶ/ር አበበ ተስፋሁን እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በአቶ ሰለሞን አሰሙ በዝርዝር ቀርበው በተጋባዥ ገምጋሚዎችና በሚመለከታቸው መምህራን አንዳንድ የማስተካከያ ሃሳቦች ቀርበው ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ካሉ ኮሌጆች አንዱ የነበረው የቴክኖሎጂ ኮሌጅ አሁን የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሚል ስያሜ ሰኔ 22 /2009 ዓ.ም በሴኔት ውሳኔ ቀይሯል፡፡ ኮሌጁን ወደ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለመቀየር የሰራተኞች የትምህርት ደረጃ (staff profile) አስፈላጊ እንደሆነ በውይይቱ ተነስቷል፡፡ ተጠሪነቱም ለፕሬዝዳንቱ ሲሆን ከአካዳክ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር ትይዩ የሆነ ሳይንሳዊ ዳይሬክተር ያለው፣ በስሩም ምክትል ዳይሬክተር፣ ሳይንቲፊክ ማኔጅመንት፣ ዲን እና የመሳሰሉት መዋቅሮች ይኖሩታል፡፡ በስሩ የነበሩ የትምህርት ክፍሎችም ወደ ት/ቤት ያድጋሉ፣ የትምህርት ክፍል ሃላፊ (department head) የሚባለው ደግሞ ወደ ስትሪም (stream) የሚያድግ ሲሆን በጀቱም ቀጥታ ከፌደራል መንግስት እንደሚበጀትለት ተገልጧል፡፡ በአጠቃላይ ስያሜው ሀገሪቱ የምትፈልገውን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና የሰው ሃይል ለማፍራት ዩኒቨርሲቲው በአጭር ጊዜ ዉስጥ እድገት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡

# በምስራቅ ጎጃም ዞን የእንግጫ ነቀላ ሥነ-ሥርዓት ተካሄደ

በወርቅነሽ ደመም




የእንግጫ ነቀላ ስነ-ስርዓት ከፊል ገጽታ

የምስራቅ ጎጃም ዞን ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ጋር በመተባበር የእንግጫ ነቀላ ሥነ-ስርዓት በባህላዊ ጭፈራና ክዋኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ተከበረ፡፡

የምስራቅ ጎጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወ/ሮ ውድአለም አልማው የበዓሉ አከባበር ዋናው አላማ እየጠፋና እየተረሳ ያለውን ባህል ለሌላው ማህበረሰብ ማስተዋወቅ፣ ማሳደግና ለተተኪ ትውልድ እንዲሸጋገር ለማድረግ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ይህ በዓል በ2008 ዓ.ም. ከማይዳሰሱ ቅርሶች ላይ የተመዘገበና ቀደም ባሉት ጊዜያት በአዲስ አመት መዳረሻ ላይ በጳጉሜ ወር በወጣቶችና ልጃገረዶች ይከወን የነበረና የራሱ የሆነ ባህላዊ ጭፈራን ክዋኔ ያለው ሲሆን በተወሰኑ የወረዳ ቀበሌዎች ላይ ያለ ቢሆንም በብዙ አካባቢዎች ግን በመጥፋት ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የበአሉ አከባበር ሲታይም ወጣቶችና ልጃገረዶች በመጀመሪያ ጥሩ የሆነ ህብረ ዜማና ክዋኔ እየከወኑ ወደ መስክ በመሄድ የእንግጫ ሳር በመንቀል ይጐነጉናሉ፡፡ በመቀጠልም የጐነጐኑትን ሳር እየሰጡ አዲሱ ዓመት መድረሱን ሲያበስሩ በአባቶች ደግሞ የእንኳን አደረሳችሁ ምርቃት ይቀበሉበታል፡፡ በመጨረሻም ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ቤተከርስትያኑን እየዞሩ ባህላዊ ጭፈራውንና ክዋኔውን ከከወኑ በኋላ በአባቶች ምርቃት ተደርጐ የበዓሉ ስንብት እንደሚሆን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይህ በዓል በደብረ ማርቆስ ከተማ ንጉስ ተክለሃይማኖት አደባባይ ከበርካታ ቀበሌዎች በመጡ የተለያዩ ቡድኖች በባህላዊ ጭፈራና ክዋኔ ደምቆ ጳጉሜ 6/2009 ዓ.ም. በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ጋር በመሆን በጮቄ ተራራ የችግኝ ተከላ አከናወነ

*በስማቸው አየነው*



*የችግኝ ተከላ ስራው ከፊል ገፅታ*

በጮቄ ተፋሰስ የምርምር ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በጮቄ ተራራ ላይ የአቫዛኾ አባጅሜ ተፋሰስ የችግኝ ተከላ ስራ አከናወኑ፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የጮቄ ተፋሰስ የምርምር ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር መስፍን አባተ እንደገለፁት በጮቄ ተራራ ላይ የችግኝ ተከላ ስራ መስራት ያስፈለገበት ምክንያት በዋናነት የጮቄ ተራራ የብርቅዬ አዕዋፋት፣ እንስሳት እና እፅዋት መገኛ ስለሆነ እንዲሁም የበርካታ ትንንሽና ታላላቅ ወንዞች መፍለቂያ ምንጭ በመሆኑ፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ለተፋሰሱ አካባቢዎችና ለህዳሴው ግድብ በርካታ ጠቀሜታዎች በመስጠትና በአጠቃላይ የበርካታ ብዝሃ ህይወት መገኛ የሆነ ቦታ በአሁኑ ወቅት በርካታ ስጋቶች ስለተጋረጡበት ያን የማዳን ሥራ ነው፡፡ አካባቢው እየተራቆተ መምጣት፣ የተፈጥሮና አገር በቀል እፅዋት መጥፋት፣ በርካታ የውሀ ክምችት ያለባቸው ቦታዎች ውሃ መያዝ አቅም እየቀነሰ መምጣት፣ የአፈር መከላትና የምንጮች መቀነስ በዋናነት የሚጠቀሱ ስጋቶች ሲሆኑ ለእነዚህ ችግሮች መከሰትና መባባስ ደግሞ በአካባቢው ህገወጥ የእርሻ መሬት መስፋፋት እና የልቅ ግጦሽ መስፋፋት የጎላውን ድርሻ ይወስዳሉ በማለት ተናግረዋል፡፡

እነዚህንና መሰል ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ አገር በቀል ችግኞችን በመትከል እና አካባቢውን ከከብት ንክኪ ነፃ በማድረግ የአካባቢው ማህበረሰብ ጮቄን መንከባከብ እንዲችል ለማድረግና በስነ-ምህዳር ጥበቃ ስራ ባለድርሻ አካላት የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ለተሳታፊዎችና አካባቢው ነዋሪዎች ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም በተከለለው ቦታ ማህበረሰቡ ሳር እያጨደ እንስሳቱን መመገብ እንዲችል ማድረግ እንዲሁም በሌሎ የአትክልትና ፍራፍሬ ስራዎች እንዲሰማሩ በማድረግ አማራጭ ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል በማለት ገልፀዋል፡፡



በ2008 ዓ.ም የክረምት ወራት በተሸረሸረ ቦረቦር መሬት የተተከሉት የኮሶ፣ ወይራና ሌሎች ሃገር በቀል ዛፎች



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በችግኝ ተከላው የተሳተፉ መምህራንና ሰራተኞ እንደገለፁት በዚህ አካባቢ የችግኝ ተከላ ስራ መሰራቱ አካባቢው የእምቅ ዉሃ መገኛ በመሆኑ ተጠብቆ እንዲዘልቅ ለማድረግ፣ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለማነሳሳት እና ስነምህዳሩ እንዲጠበቅ በማድረግ በኩል ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል፡፡ በቀጣይም የተተከሉ ችግኞች እንዲያድጉ መንከባከብ እና ከከብቶች ንክኪ ማራቅ ተገቢ መሆኑን ገልፀው ይህ አይነት ስራ በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የችግኝ ተከላ ስራ የተሰራበት የአቫዛዥ አባጅሜ ተፋሰስ ቀበሌ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ በእውቀት አያሌው እየተመናመነ የመጣው የጮቄ ተራራ ብዝሃ ህይወት ተመልሶ እንዲያገግም የችግኝ ተከላ ስራ መሰራቱ ተገቢ መሆኑን ገልጸው በቀጣይም ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር እና በአደረጃጀት የመንከባከብና ጥበቃ የማድረግ ስራ እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም የምስ/ጎጃም ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ተመስገን ጥሩነህ የአካባቢው ማህበረሰብ የተተከለውን ችግኝ መንከባከብ፣ ከከብት ንክኪ ነፃ በማድረግ እንዲሁም የተፈጥሮ እፅዋትን በመጠበቅ በጮቄ ላይ የተደቀኑትን ፈተናዎች/ስጋቶች መቀነስ እንዲችሉ እና አማራጭ የኢኮኖሚ ምንጮችን በመስራት፣ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ዘዴዎችን መከተል፣ ዘመናዊ የእንስሳት አመጋገብን መጠቀምና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ልዩ ትኩረት በመስጠት ተከታታይ ውይይት ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል፡፡

በዕለቱ በ2008 ዓ.ም ተመሳሳይ ወቅት ቦረቦር መሬት ላይ የተተከሉትን ችግኞች በመጎብኘት የመኮትኮት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ዛፎቹ የአፈር መሸርሸርን በመከላከል ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅዖ ከፍተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይም ተመሳሳይ የሆነ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮችን ከማዘጋጀት ጎን ለጎን ለአካባበው አርሶ አደርና የከተማው ማህበረሰብ የዛፍ ችግኞችን በማፍላት የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር መጠበቅ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# Leaders' Forum Evaluates the report of 2009 Plan Execution



Partial view of Leaders Forum

DMU: Debre Markos University has conducted leaders' forum to evaluate the implementation of the budget year plan under the Presence of the university leaders on August 4/2017.

The Evaluation was led by Dr. Nigussie Mitiku, Debre Markos University President, whereas the yearly report was reported by Aklilu Getachew, program design, monitoring and evaluation expert in the University.

The report contained the overall activities implemented in the year substantially. On the same token, the cognitive, psychomotor, affective and material input constraints as well practitioners' implementation weakness and strength have also been screened out.

Quality education, research and community service vis-a-vis good governance, coordination and partnerships aiming to promote students and staff benefit and enhancing the satisfaction level of customers were projected during the report.

Organizing educational development army has been done in the preliminary, implementation and closing chapters of the fiscal year effectively. Cooperative working, strong personnel, adequate input, coordinated leadership mythology were noticed to how achieve quality education sustainably.

The exemplary practices of the year are plan-oriented implementation, cooperativeness, the presence of updated trainings, enhancement of female teachers' leadership and research skills, and conduct researches in groups. There are also some limitations and problems, which are taken as a lesson to improve in the coming year accomplishments. On the report, assuring quality education, reducing attrition rate, improving the participations of female students', empowering problem solver researches, offering community service, strengthening national and foreign relations, following and appraising projects have seen as homework of the university.

Eventually, taking the closing year implementation in to consideration, the 2010 budget year plan is discussed and endorsed massively.

# Debre Markos University Distributes New Improved Grass Species to Farmers



Site of improved grass

DMU: Debre Markos University Animal Science Department distributed the newly improved grasses to the surrounding farmers. The distribution was taking place at four Gozamin Woreda kebeles from August 17-18/2017 and noticed that more than 85,200 single Densho and Setariya grass species were distributed with the presence of experts of the woreda and kebeles.

Assistant Professor in the department of Animal Science of Debre Markos University Dr. Birhanu Alemu States to the experts and farmers about the newly improved grass, as it has double roles. The newly improved grass is important to keep the animal production for cattle on one hand and conserve the soil from erosion on the other hand. Furthermore, it plays significant role for animals feed confidently.

For that matter, Debre Markos University compound beautification directorate prepares grass nursery in the compound which exceeds ten permanent grass species bringing from Finoteselam, Sinan woreda, Bahir Dar University and other nearby woredas, Dr. Birhanu added.

It was noticed that the improved grasses are able to grow everywhere where little water abundant with fragmented plot of land. Then, talking with the zone Animal Science sector in depth the university has a plan to distribute the grass to many areas. Lastly, the grass could be to every cattle/ animals and therefore it is advised to feed the grass periodically to keep the nutrients of the grass.

Gozamine woreda Animal Science Sector representative Ato Esuyawokal Tiruneh expresses that Gozamin woreda especially the kebeles that the grass has been distributed are the special localities where adequate cattle are found and known for cattle breeding. Therefore, the grass is advisable to be distributed for famers to feed their cattle with some plot of land, he added.

In the end, Debre Markos University promised to work with the interested woredas to distribute grasses elsewhere. On this condition the woredas should involved plans to bring their maximum usage more than 50%, on this regard, DMU, is also witness to be on behalf of them.



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# Debre Markos University hosts a workshop on push-pull technology



DMU: Debre Markos University Conducts workshop to implement push-pull technology in order to combat stunting weeds. Works are also done to disseminate biogas technology to the massive users at most.

Dr. Getnet Atinafu, Research and technology transfer directorate director in Debre Markos University, officially announces the participants and the objective of the workshop held at the moment.

Assistant professor Gent Degu, Vice President for Research and Community Service Vice President of Debre Markos University states that Debre Markos University is carrying out its prominent activities of community service program after screening the problem tangibly and critically via scientific reserach.

On this regard, to get rid of problem observed in maize production once and for all, Debre Markos University conducts the workshop occurred on the selected East and West Gojjam Zone districts. Furthermore, Agricultural Sectors, Cooperative organs, farmers, experts from Debre

Markos University and others also participate to adopt and use the technology actively, she added.

During the occasion, Dr. Tewoldebirhan Gebreegziabhier, Cooperative Organ in the institute of Sustainable Development, narrates that the workshop is crucial to reduce soil erosion to preserve the ecological system of the land and to improve the natural agriculture systems by increasing the fertility of soil, productivity of crops and to preserve the soil nutrients from the earth surface dealing with the nature of the land rationally.

The helping organ from institute of sustainable Development and Tewolde G/Egziabher wife, Sue Edwards on her side states that agriculture is a complex system of activties so that everybody ought to employ technology that enhances productivity and fertility of soil to bring green economy as of their forefathers did.

The members of the project from Debre Markos University Dr. Mesfin Abate and Dr. Birhanu Alemu have presented the detailed description of push- pull technology implementation from the theoretical perspective to its implementation. Maize is highly produced in Eastern and Western Gojjam Zones. However, it's highly harmed by stunting weeds, which reduces the production from time to time. Due to this fact, being with other universities and cooperative organs/ institutions, Debre Markos University is also implementing push-pull technology to eliminate the problems and to increase soil fertility. The technology is called strip cropping, they explained rationally. Mr. Nigussie Habtemariam, the member organ of the project, clearly elaborates about biogas implementation. Regarding, questions were raised and ample responses were raised accordingly.

Debre Markos University Agriculture and Natural Resource college staffs, Eastern and western Gojjam Zone selected woreda concerned bodies, woreda and zone administrators, cooperation organs, Debre Markos University research team organs, farmers and others were participants in the workshop.

Finally, the participants observed the field trip to 'Abalibanos Kebele, Gozamin woreda to have a look at the push-pull technology and the biogas preparation.

# Debre Markos University Launches more than ten New Under and Postgraduate Programmes in 2010

Under and postgraduate programmes curricula are presented to the senate of the university, which is held on October 9/2017, and approved to be launched three undergraduate and eight postgraduate programmes in 2010 academic year. The senate approves these curriculums upon the profile of staffs to deliver the programmes.

The undergraduate programmes are BA in Theatrical Art, BSC in Anesthesia, and BSc in Environmental Health. The postgraduate programmes are presented and approved by the university senate. The approved postgraduate programmes are MSc in Integrated Watershed Management, MSc in Agronomy, MSc in Computer Engineering, MSc in Information technology, MSc in Hydraulic Engineering, MSc in Maternity and Reproductive Health, MSc in Botanical Science and MA in History.

During the curriculum review, it is stated that programmes are designed upon the findings of need assessments conducted on their respective departments. The education quality assurance mechanisms have great emphasis to get the approval of the senate.

